# ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ

## የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ

ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ

የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መበል 27 ዓመት ቑ.2 መቐለ 333/2012ዓ/ም

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝወፀ

27ኛ ዓመት ቁ.2 መቐለ 333/2012ዓ/ም


## አወዳደባ፣ ስልጣንን ተግባርን ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ንምውሳን ዝወፀ አዋጅ ቁፅሪ 333/2012 ዓ.ም

ብመሰረት ሕገ መንግስቲ ዝተጣየሸ ነፃ ስርዓት ዳይነት ዘመሓድሮ ናይ ባዕሉ ኣካል ከምዝህልዎ ሕገ መንግስቲ ስለ ዝድንግግ፣

ነፃነት ዳይነትን ተሓታትነትን ብምጥንኻር መሰልን ግቡእን ዳያኑ፣ ሬጅስትራራትን ተሸየምቲ ጉባኤን ሚዛኖም ሓልዮም ክትግበሩ ብምግባር ወሳናይ ተርኡ ዝፃወት ብመትከላት ሕገ መንግስቲ ዝምራሕ፣ ግዕዝይና ዘይፃወር፣ ግልፅነት ዝዓሰሎ ውፅኢታውን ስሉጥን ግልጋሎት ብምሃብ ህዝባዊ ኣመኔታ ዘትረፈ ስርዓት ዳይነት ንምህናፅ ዘኽእሎ ኣወዳድባን ስልጣንን ከም ብሓዱሽ-ምውሳን አድላይ ኮይኑ ብምርካቡ፣

አዋህባ ግልጋሎት ዳይነት ጠለብ ህዝቢ ንምምላእ ትፅቢት ኣብ ዝግበረሉ ብርኪ ንክበፅሕ ምሕደራ ስርዓት ዳይነት ተመጣጣንን ውፅኢታውን ብዝኾነ መንገዲ ምውዳቡ አድላይ ምኳኑ ብምእማን፣

ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ብመሰረት ተመሓይሹ ዝወፀ ሕገ መንግስቲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዓንቀፅ 49/3/ሀ/ እዚ አዋጅ አውፂኡ ኣሎ።

## የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 333/2012

በሕገ መንግስት መሰረት የተቋቋመው የዳኝነት ስርዓት የሚያስተዳድረው የራሱ አካል እንደሚኖረው ሕገ መንግስቱ ስለ ሚደነግግ፣

የዳኝነት ነፃነትና ተጠያቂነትን በማጠናከር የዳኞች፣ ሬጅስራሮችና የጉባኤ ተሿሚዎች መብትና ግዴታ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንዲተገበሩ በማድረግ ወሳኝ ሚናውን የሚጫወት፣ በህገ መንግስቱ መርሆች የሚመራ፣ ሙስናን የማይሸከም፣ ግልፅነት የነገሰበት፣ ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ህዝባዊ አመኔታ ያተረፈ የዳኝነት ስርዓት ለመገንባት የሚያስችለውን አደረጃጀትና ስልጣን እንደ አዲስ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የህዝቡን ፍላጎት ለማሟላት በሚጠበቀው ደረጃ እንዲደርስ የዳኝነት ስርአቱ ተመጣጣኝና ውጤታማ በሆነ መንገድ መደራጀቱ አስፈላጊ መሆኑ በማመን፣

የትግራይ ክልል ብሄራዊ ክልላዊ ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት ዓንቀፅ 49/3/ሀ/ መሰረት ይህ አዋጅ አውጥተዋል።

## ክፍሊ ሓደ

## ሓፈሻዊ ሕጋገ

**ዓንቀፅ 1.** **ሓጺር ርእሲ**

እዚ ኣዋጅ "ስልጣንን ተግባርን ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ንምውሳን ዝወፀ ኣዋጅ ቁፅሪ ---/2012" ተባሂሉ ክፅዋዕ ይኽእል።

**ዓንቀፅ 2.** **ትርጉም**

ኣገባብ እቲ ቃል ካሊእ ትርጉም ዘውህቦ እንተዘይኮይኑ ኣብዚ ኣዋጅ እዚ፡-

1."**ክልል**"ማለት ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።

2."**ሕገ መንግስቲ**" ማለት ተመሓይሹ ዝወፀ ሕገ መንግስቲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።

3."**ቤት ምኽሪ**" ማለት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።

4."**ቤት ፍርዲ**" ማለት ላዕለዋይ፣ ማእኸላይን ወረዳን ኣብያተ ፍርዲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዘጠቓልል እዩ።

5."**ጉባኤ**" ማለት ብመሰረት እዚ ኣዋጅ ብብርኪ ክልል ዝተጣየሸ ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።

6."**ቤት ፅሕፈት ጉባኤ**" ማለት ስራሕቲ ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ንክሳልጥ በዚ ኣዋጅ ዝተጣየሸ ሕጋዊ ሰውነት ዘለዎ ኣካል እዩ።

7."**ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ**" ማለት ንቤት ፅሕፈት ጉባኤ ክመርሕ ብኣካቢ እቲ ጉባኤ መቕረባይነት በቲ ጉባኤ ዝሽየም ብዓል ሞያ ሕጊ እዩ።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀፅ 1.** **አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ " የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር ---/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀፅ 2.** **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ኣዋጅ ውስጥ፡-

1."ክልል" ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነው ።

2."**ህገ-መንግስት**" ማለት ተሻሽሎ የወጣው የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት ነው።

3."**ምክር ቤት**" ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ነው።

4."**ፍርድ ቤት**" ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፣ ከፍተኛ እና ወረዳ ፍርድ ቤቶችን የሚያጠቃልል ነው።

5."**ጉባኤ**" ማለት በዚህ ኣዋጅ መሰረት የተቋቋመ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ነው።

6."የ**ጉባኤ ፅሕፈት ቤት**" ማለት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ስራዎችን ለማቀላጠፍ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው።

7."**የጉባኤ ፅሕፈት ቤት ሓላፊ**" ማለት የጉባኤ ፅሕፈት ቤትን ለመምራት በጉባኤው ሰብሳቢ አቅራቢነት በጉባኤው የሚሾም የሕግ ባለሙያ ነው።

8."ዳይና" ማለት ብጉባኤ ተመልሚሉ ብዳይነት ኣብ ቤት ፍርዲ ንክሰርሕ ብቤት ምኽሪ ዝተሾመ በዓል ሞያ ሕጊ እዩ።

9."መሰረታዊ ስራሕ ዳይነት" ማለት ፋይል ተኸፊቱ ናብ መጋባእያ ካብ ዝቐረበሉ ክሳብ ውሳነ ዝወሃበሉ ከምኡ እወን ኣፈፃፀም ክሲ ተኸፊቱ መዝገብ ዕልባት ክሳብዝወሃበሉ ዘሎ ስራሕ ዳይነት ዘጠቓልል እዩ።

10."ተሸያሚ ጉባኤ" ማለት ፕረዚደንትን ምኽትል ፕረዚደንትን ማእኸላይ ቤት ፍርዲ፣ ፕረዚደንት ወረዳ ቤት ፍርዲ፣ ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ፣ ዋና ሬጅስትራር ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ፣ ሓላፊ ክፍሊ ሬጅስትራር ማእኸላይ ቤት ፍርዲ፣ ዳይሬክተር ብቕዓት ሞያ፣ መፅናዕትን ምርምርን፣ ዳይሬክተር ስነ ምግባርን ኢንስፔክሽንን ካልኦትን ኮይኖም ብመቕረባይነት ኣካቢ ጉባኤ ብጉባኤ ዝሸየም ኣመራርሓ እዩ።

11. "ሬጅስትራር" ማለት ብጉባኤ ተመልሚሉ ብሬጅስትራርነት ኣብ ቤት ፍርዲ ንክሰርሕ ብቤት ምኽሪ ዝተሾመ በዓል ሞያ እዩ።

12."ሕፁይ ዳይና" ማለት ብጉባኤ ምስተመልመለ ብቤት ምኽሪ ክሳብ ዝሸየም ብሞያ ሕጊ ኣብ ቤት ፍርዲ ብግዝያውነት ተመዲቡ ዝሰርሕ ብዓል ሞያ ሕጊ እዩ።

13. "ሕፁይ ሬጅስትራር" ማለት ቤት ፅሕፈት ጉባኤ ዝህቦ መፍለይ ፈተና ምስ ሓለፈ ብቕዓቱ ብጉባኤ ተኣሚንሉ ናብ ቤት ምክሪ ንሽመት ክሳብ ዝቐርብ ብፈተነ ስራሕ ሬጅስትራርነት ኣብ ቤት ፍርዲ ተመዲቡ ዝሰርሕ በዓል ሞያ

8."ዳኛ" ማለት በጉባኤ ተመልምሎ በፍርድ ቤት በዳኝነት እንዲሰራ በምክር ቤት የተሾመ የሕግ ባለሙያ ነው ።

9."መሰረታዊ የዳኝነት ስራ" ማለት ፋይል ተከፍቶ ችሎት ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ውሳኔ እና የአፈፃፀም መዝገብ ተከፍቶ እልባት እስኪሰጠው ያለውን የዳኝነት ስራ የሚያጠቃልል ነው።

10."የጉባኤ ተሿሚ" ማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕረዚደንትና ምክትል ፕረዚደንት፣ የወረዳ ፍርድ ቤት ፕረዚደንት፣ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ፅሀፈት ቤት ሃላፊ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዋና ሬጅስትራር፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሬጅስትራር ክፍል ሃላፊ፣ የሙያ ብቃት፣ ጥናትና ምርምር ዳይሬክተር፣ የስነ ምግባርና ኢንስፐክሽን ዳይሬክተር እና ሌሎች ሲሆኑ በጉባኤው ሰብሳቢ አቅራቢነት በጉባኤው የሚሾም አመራር ነው።

11."ሬጅስትራር" ማለት በጉባኤ ተመልምሎ በፍርድ ቤት በሬጅስትራርነት እንዲሰራ በምክር ቤት የተሾሙ ባለሙያ ነው ።

12."እጩ ዳኛ" ማለት በጉባኤው ከተመለመለ በኋላ በምክር ቤት እስከሚሾም ድረስ በፍርድ ቤት በጊዜያዊነት ተመድቦ የሚሰራ የህግ ባለሙያ ነው

13."እጩ ሬጅስትራር" ማለት የጉባኤው ፅሕፈት ቤት የሚሰጠውን መመዘኛ ፈተና ካለፈ በኃላ ብቃቱ በጉባኤው ታምኖበት ወደ ምክር ቤት ለሹመት እስኪቀርብ ድረስ በሙከራ በሬጅስትራርነት ስራ በፍርድ ቤት ተመድቦ

እዩ ።

14."ጉድለት ስነ-ምግባር" ማለት ኣብ ደንቢ መተሓዳደርን ስነ ምግባርን ዳያኑ፣ ሬጅስትራራትን ተሸየምቲ ጉባኤን ጉድለት ስነ ምግባር ተባሂሎም ካብ ዝተዘርዘሩ ውሽጢ ሓደ ወይ ካብኡ ንላዕሊ ሕጋገ ዝጥሕስ ተግባር'ዩ።

15."ርኡይ ዝኾነ ናይ ስራሕ ብቕዓትን ቅልጣፈን ምንኣስ" ማለት ጉባኤ ብዘውፅኦ መዕቀኒ ኣፈፃፅማ ስራሕ መሰረት ተመዚኑ ጉባኤ ካብ ዘቐመጦ ዝነኣሰ ውፅኢት ንታሕቲ ዘምፅእ ዳይና፣ ሬጅስተራር፣ ወይ ተሸያሚ ጉባኤ እዩ።

16. "ሰብ" ማለት ናይ ተፈጥሮ ሰብ ወይ ሕጋዊ ሰብነት ዝተወሃቦ ኣካል እዩ።

**ዓንቀፅ** 3. **ኣገላልፃ ፆታ**

ኣብዚ ኣዋጅ ብተባዕታይ ፆታ ዝተሓገገ ንኣንስተይቲ ፆታ'ውን ዝሓውስ'ዩ።

**ዓንቀፅ** 4. **ወሰን ተፈፃምነት**

እዚ ኣዋጅ ኣብ ቤት ፍርዲ ኣብ ምስራሕ ዝርከብ ዳይና፣ ሬጅስትራር፣ ተሸያሚ ጉባኤ፣ ሕፁይ ዳይናን ሕፁይ ሬጅስትራርን ተፈፃሚ ይኸውን።

**ክፍሊ ክልተ**

**ኣጣይሻ፣ ኣወዳድባ፣ ስነ ስርዓት ኣኼባን ዘመን ስራሕን ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ**

**ዓንቀፅ** 5. **ኣጣይሻን ኣወዳድባን**

ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ክልል ትግራይ ድሕሪ ሕዚ "ጉባኤ" እናተባሃለ ዝፅዋዕ በዚ ኣዋጅ ብሓዱሽ መልክዕ ተጣይሹ ኣሎ።

የሚሰራ ባለሙያ ነው።

14."የስነ-ምግባር ጉድለት' ማለት በዳኞች፣ ሬጅስትራሮችና ጉባኤ ተሿሚዎች መተዳደሪያና የስነ ምግባር ደንብ ውስጥ የስነ ምግባር ጉድለቶች ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ድንጋጌ የሚጥስ ተግባር ነው።

15"ጉልህ የሆነ የስራ ብቃትና ቅልጣፌ ማነስ" ማለት ጉባኤው በሚየወጣው የስራ አፈፃፀም መመዘኛ መሰረት ተመዝኖ ጉባኤው ካስቀመጠው ዝቅተኛ ውጤት በታች ያመጣ ዳኛ፣ ሬጅስትራር ወይም የጉባኤ ተሻሚ ነው።

16"ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

**አንቀፅ** 3. **የፆታ አገላለፅ**

በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

**አንቀፅ** 4.**የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በፍርድ ቤት በመስራት ላይ የሚገኝ ዳኛ፣ ሬጅስትራር፣ የጉባኤ ተሿሚ፤ እጩ ዳኛና እጩ ሬጅስትራር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

**ክፍል ሁለት**

**የዳኞች አሰተዳደር ጉባኤ አመሰራረት፣ አደረጃጀት፣ የስብሰባ ስነ ስርዓትና የስራ ዘመን**

**አንቀፅ** 5.**አመሰራረትና አደረጃጀት**

የትግራይ ክልል የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ከዚህ በኋላ "ጉባኤ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ በአዲስ መልክ ተቋቁሟል።

**ዓንቀፅ 6. ስነ-ስርዓት ኣኼባ ጉባኤ**

1. ስሩዕ ኣኼባ ጉባኤ ኣብ ወርሒ ሓደ ግዘ ይኸውን።
2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተሓገገ ሕልው ኮይኑ ከምኣድላይነቱ ሓደ ሲሶ ኣባላት ጉባኤ እንትሓቱ ወይ ኣካቢ ጉባኤ መእመናይ ምኽንያት እንትረኺቡ ህፁፅ ኣኼባ ክፅውዕ ይኽእል። ዝርዝሩ ብመምርሒ ይውሰን።
3. ክልተ ሲሶ ኣባላት ጉባኤ እንትርከቡ ምልኣተ ጉባኤ ይኸውን።
4. ናብ ጉባኤ ዝቐርብ ዋኒን ብዝተረኸቡ ኣባላት ጉባኤ ኣብዝሓ ድምፂ ይውሰን፤ ድምፂ ኣባላት ማዕረ ኣብ ክልተ ዝተመቐለ እንተኾይኑ ኣካቢ ዝደገፎ ሓሳብ ሰዓራይ ይኸውን።
5. ኣካቢ ጉባኤ ኣብ ዘይህልወሉ እዋን ምክትል ኣካቢ ጉባኤ ተኪኡ ይሰርሕ።

**ዓንቀፅ 7. ምዕቃብ ምሽጥራውነት ጉባኤ**

1. ጉባኤ ዕላዊ ዘይገበሮ ሓሳብ፣ ክትዕ፣ ወይ ውሳነ ብምሽጥር ይትሓዝ።
2. ዝኾነ ኣባል ጉባኤ ወይ ኣብ ኣኼባ እቲ ጉባኤ ዝተሳተፈ ሰብ ነዚ ምሽጥር ናይ ምዕቃብ ግቡእ ይህልዎ።

**ዓንቀፅ 8. ዘበን ስራሕ**

1. ዘበን ስራሕ ኣባል ጉባኤ ሓሙሽተ ዓመት ኮይኑ ንተወሳኺ ሓደ ዘበን ስራሕ ጥራሕ ዳግም ክምረፅ ይኽእል።
2. መራፂ ኣባል እምነት ንዝሰኣነሉ ብዳያት ዝተወከለ ኣባል ጉባኤ ናይ ስራሕ ዘበኑ

**አንቀፅ 6. የጉባኤው የስብሰባ ስነስርዓት**

1. የጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደየአስፈላጊነቱ አንድ ሶስተኛ የጉባኤው አባላት ሲጠይቁ ወይም የጉባኤው ሰብሳቢ አሳማኝ ምክንያት ሲያገኝ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል።
3. ሁለት ሶስተኛ የጉባኤው አባላት ሲገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።
4. ለጉባኤው የሚቀርብ ጉዳይ ከተገኙት የጉባኤው አባላት ብአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፣ የአባላቱ ድምፅ እኩል በሁለት የተከፈለ ከሆነ የጉባኤው ሰብሳቢ የሚደግፈው ሃሳብ አሸናፊ ይሆናል።
5. የጉባኤው ሰብሳቢ በማይገኝበት ጊዜ የጉባኤው ምክትል ሰብሳቢ ተክቶ ይሰራል።

**አንቀፅ 7. የጉባኤው ምስጢራዊነት መጠበቅ**

1. ጉባኤው ይፋ ያላደረገው ሃሳብ ፣ ክርክር ወይም ውሳኔ በምስጢር ይያዛል።
2. የጉባኤው አባል ወይም በጉባኤው ስብሰባ የተሳተፈ ሰው ምስጢሩን የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት።

**አንቀፅ 8. የስራ ዘመን**

1. የጉባኤው አባል የስራ ዘመን አምስት ዓመት ሲሆን ለተጨማሪ አንድ የስራ ዘመን ብቻ እንደገና ሊመረጥ ይችላል።
2. መራጩ አባል እምነት ያጣበትን የዳኞች ተወካይ የጉባኤ አባል የስራ ዘመኑ ሳያልቅ

ከይተወደአ ካብ ኣባልነት ከውርዶ ይኽእል።

3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝተሓገገ ተፈፃሚ ዝኸውን ሓደ ሲሶ መራሒ ኣባል ብፊርማ ኣጀንዳ ክተሓዘሉ ምስ ገበረ ብኣብዝሓ ድምፂ መራሒ ኣባል እንትውሰን እዩ።

4. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝተደንገገ እንተሃለወ እኳ ብመሰረት እዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 15 ንኡስ ዓንቀፅ 4 ድሕሪ መረፃ ንዝጎደለ ኣባል ጉባኤ ንምምላእ ዝተመረፀን ትሕቲ ክልተ ዓመት ብኣባልነት ዘገልገለን እንተኾይኑ ንሓደ ስራሕ ዘበን ብኣባልነት ከምዝፀንሐ ኣይቑፀርን።

ከአባልነት ሊያወርደው ይችላል።

3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ተፈፃሚነት የሚኖረው የመራጩ አባል አንድ ሶስተኛ በፊርማው አጀንዳ እንዲያዝለት በመራጩ አባል አብላጫ ድምፅ ሲወሰን ነው።

4. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 15 ንኡስ አንቀፅ 4 መሰረት ከምርጫ በኋላ ለጎደለው አባል ጉባኤ ለማሟላት የተመረጠና ከሁለት ዓመት በታች በአባልነት ያገለገለ ከሆነ ለአንድ የስራ ዘመን በአባልነት እንደ ሰራ አይቆጠርም።

## ክፍሊ ሰለስተ

## ተዋፅኦ ኣባላትን ስልጣንን ጉባኤ

### ዓንቀፅ 9. ኣባላት ጉባኤ

እቲ ጉባኤ እዞም ዝስዕቡ ተዋፅኦ ኣባላት ይህልውዎ።

1. ፕረዚዳንት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ.................................. ኣካቢ
2. ምኽትል ፕረዚዳንት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ........................ምኽትል ኣካቢ
3. ሰለስተ ፕረዚደንታት ማእኸላይ ቤት ፍርዲ......................................ኣባል
4. ሓደ ዳይና ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ.................................... ኣባል
5. ክልተ ዳያኑ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ..........................................ኣባል

## ክፍል ሶስት

## የጉባኤው የአባላት ተዋፅኦና ስልጣን

### አንቀፅ 9.የጉባኤው የአባላት

ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የጠቅላይ ፍርድቤት ፕረዚዳንት ....................................................ሰብሳቢ
2. የጠቅላይ ፍርድቤት ምክትል ፕረዚዳንት...........................ምክትል ሰብሳቢ
3. ሶስት የከፍተኛ ፍርድቤት ፕረዚደንቶች ...................................አባል
4. አንድ የጠቅላይ ፍርድቤት ዳኛ............. አባል
5. ሁለት የከፍተኛ ፍርድቤት ዳኞች ...............................................አባል

6. ሰለስተ ዳያኑ ወረዳ ቤት ፍርዲ ......ኣባል
7. ዋና ሬጅስትራር ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ......................................ኣባል
8. ሰለስተ ኣባላት ቤት ምኽሪ ............................... ኣባል
9. ሓላፊ ቢሮ ፍትሒ ክልል ................... ኣባል
10. ሓላፊ ቢሮ ፀጥታ ምምሕዳርን ክልል .................ኣባል
11. ኣቦ መምበር ማሕበር ሓረስቶት ትግራይ............................... ኣባል
12. ኣቦ/ኣዶ መምበር ማሕበር መናእሰይ ትግራይ...............................ኣባል
13. ኣዶ መምበር ማሕበር ደቂ ኣንስትዮ ትግራይ ............................... ኣባል
14. ኣቦ/ኣዶ መምበር ማሕበር ጠበቓታት ትግራይ ተወካሊ...................... ኣባል

**ዓንቀፅ10. <u>ኣመራርፃን ረቛሕን ኣባላት ጉባኤ</u>**

1. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 9 ንኡስ ዓንቀፅ 3፣ 5ን 6ን ብዝተደንገገ መሰረት ንኣባልነት ጉባኤ ንክምረፅ ፦
   ሀ. ሰለስተ ዓመትን ልዕሊኡን ብስራሕ ዳይነት ዘገልገለ፤
   ለ. ብስነ-ምግባሩን ኣፈፃፅማ ስርሑን ምስጉን ዝኾነ፤
   ሐ. ኣባል ጉባኤ ኾይኑ ንከገልግል ፍቃደኛ ዝኾነ ፤

6. ሶስት የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ............አባል
7. የጠቅላይ ፍርድቤት ዋና ሬጅስትራር .......................................አባል
8. ሶስት የምክርቤት አባላት ...........................................አባል
9. የክልሉ የፍትህ ቢሮ ሃላፊ ................................አባል
10. የክልሉ የፀጥታ እና አስተዳደር ቢሮ ሃላፊ .......................አባል
11. የትግራይ ገበሬዎች ማሕበር ሊቀመንበር........................................አባል
12. የትግራይ ወጣቶች ማሕበር ሊቀ መንበር.............................................አባል
13. የትግራይ ሴቶች ማህበር ሊቀመንበር.........................................አባል
14. የትግራይ ጠበቆች ማህበር ሊቀመንበር ......................................................አባል

**አንቀፅ 10. <u>የጉባኤው አባላት አመራረጥና መመዘኛ</u>**

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 3፣ 5 እና 6 በተጠቀሱት መሰረት ለጉባኤ አባልነት ለመመረጥ ፦
   ሀ. በዳኝነት ስራ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገለ፣
   ለ. በስነ-ምግባሩና በስራው የተመሰገነ ፤
   ሐ. የጉባኤ አባል ሆኖ ለማገልገል ፈቃደኛ የሆነ፤

2. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 9 ንኡስ ዓንቀፅ 5ን6ን ካብ ዝተጠቐሱ ኣባላት ጉባኤ እንተወሓደ ሓንቲ ጓል ኣንስተይቲ ክትኸውን ኣለዋ።
3. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 9 ንኡስ ዓንቀፅ 3፣ 4፣ 5ን 6ን ብዝተፀርሐ መሰረት ዝምረፁ ኣባላት ጉባኤ በዚ ኣዋጅ ካብ ዝመሓደሩ እንተነኣሰ ክልተ ሲሶ ኣባላት ኣብ ዝተረኸብሉ ሓፈሻዊ ኣኼባ ይኸውን።
4. ድሕሪ መረፃ ናይ ውክልና ክፍተት እንተጋጢሙ፡-
   ሀ. ኣብ መጀመሪያ ወይ መወዳእታ ዓመት ኣብ ዝግበር ሓፈሻዊ ኣኼባ ዳያኑ፣ ሬጅስትራራትን ተሸየምቲ ጉባኤን ብመረፃ ክትካእ ይግበር።
   ለ. ብምኽንያት ዝተውሃበ ብርኪ ዕብየት ክፍተት ዝተፈጠረ እንተኾይኑ ዕብየት ዝረኸበ ተወካሊ መማለኢ መረፃ ክሳብ ዝካየድ ውክልንኡ ከምዘሎ ይፀንሕ።
5. ብመሰረት እዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 9 ንኡስ ዓንቀፅ 8 ካብ ቤት ምኽሪ ዝውከል ኣባል ክንዲ ዝተኻኣለ ፡-
   ሀ.ብዛዕባ ስራሕቲ ቤት ፍርዲ እኹል ኣፍልጦ ዘለዎ፤
   ለ. ብሓፈሻ ንስርዓት ፍትሒ ብፍላይ ድማ ንስርዓት ዳይነት ናብ ዝሓሸ ብርኪ ንምስግጋር ዕኑዕ እምነት፣ ድሌትን ቆራፅነትን ዘለዎን፤
   ሐ.ተዋፅኦ ደቂ ኣንስትዮ ኣብ ግምት ዘእተወን ይኸውን።

2. በዚህ አዋጅ ዓንቀፅ 5 እና 6 ከተጠቀሱት የጉባኤው አባላት መካከል ቢያንስ አንዱ ሴት መሆን አለበት።
3. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 3፣4፣ 5 እና 6 በተጠቀሰው መሰረት የሚመረጡ የጉባኤ አባላት በዚህ አዋጅ ከሚተዳደሩ ቢያንስ ሁለት ሶስተኛ አባላት በተገኙበት ጠቅላላ ስብሰባ ይሆናል።
4. ከምርጫ በኋላ የውክልና ክፍተት ሲያጋጥም፡-
   ሀ. በየዓመቱ መጀመርያ ወይም መጨረሻ በሚደረገው የዳኞች፣ ሬጅስትራሮችና የጉባኤ ተሻሚዎች ጠቅላላ ስብሰባ በምርጫ እንዲተካ ይደረጋል።
   ለ. ክፍተቱ የተፈጠረው አባሉ ባገኘው የእድገት ደረጃ ምክንያት እንደሆነ እድገቱን ያገኘ ተወካይ የሚሟያ ምርጫ እስኪካሄድ የያዘው ውክልና ይዞ ይቆያል።
5. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 8 መሰረት ከምክር ቤት የሚወከል አባል በተቻለ መጠን፡-
   ሀ. ስለ ፍርድ ቤት ስራ በቂ እውቀት ያለው፤
   ለ. በጠቅላላ ለፍትህ ስርዓቱ በተለይ ደግሞ ለዳኝነት ስርዓቱ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር ፅኑ እምነት፣ ፍላጎትና ቁርጠኝነት ያለው እና
   ሐ. የሴቶችን ተዋፅኦ ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል።

6. ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ ብዘይ ድምፂ ፀሓፊ ጉባኤ ኮይኑ ይሰርሕ።

**ዓንቀፅ 11. ካብ ኣባልነት ጉባኤ ዘልዕል ምኽንያት**

1. ሓደ ኣባል ጉባኤ ካብ ኣባልነቱ ክሰናበት ዝኽእል፡-
   ሀ. ካብ ስርሑ እንትሰናበት፤
   ለ. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 10 ንኡስ ዓንቀፅ ለ ዝተደንገገ ከም ዘሎ ኾይኑ ብዕቤት ወይ ብኻሊእ ምኽንያት ናብ ካሊእ ብርኪ ቤት ፍርዲ ዝኸይድ እንተኾይኑ፤
   ሐ. ናይ ጉባኤ ግቡእን ሓላፍነትን ብዝግባእ ዘይዋፃእ ወይ ንተኸታታሊ ሰለስተ ኣኼባታት ጉባኤ ብዘይፍቓድን ብዘይብቑዕ ምኽንያትን ዘይቀረበ ምዃኑ ጉባኤ እንትረጋገፅን በቲ ጉባኤ መጠንቀቕታ ተዋሂብዎ ከመሓይሽ እንተዘይክኢሉን፤ ወይ
   መ. በቲ ጉባኤ ብከቢድ ጉድለት ስነ-ምግባር ዝተቐፅዐ እንተኾይኑ እዩ።
2. ኣብ ኣኼባ ዘይርከብ ኣባል ጉባኤ ካብ ቤት ፍርዲ ዝተወከለ እንተኾይኑ ብመተሓዳደሪ ደንቢ ዳያኑ፣ ረጅስትራርን ተሸየምቲ ጉባኤን ከም ጉድለት ስነምግባር ተራእዩ ክሲ ጉድለት ስነ ምግባር ዝቐርበሉ ይኸውን።
3. ካብ ቤት ፍርዲ ወፃኢ ዝውክል ኣባል ጉባኤ ብዘይቡቑዕ ምኽንያት ሓላፍነቱ ዘይዋፅእ እንተኾይኑ መጀመርያ ብኣካቢ ጉባኤ ንከማሓይሽ ብቃል ይንገሮ፤ እንተዘይኣማሓይሹ ብፅሑፍ ይግለፀሉ፤ ለውጢ ተዘይኣምፂኡ ቤት ምኽሪ ክፈልጦ ይግበር።

6. የጉባኤው የፅህፈት ቤት ሃላፊ ያለ ድምፅ የጉባኤው ፀሓፊ ሆኖ ይሰራል።

**አንቀፅ 11. ከጉባኤ አባልነት የሚያስነሱ ምክንያቶች**

1. አንድ የጉባኤ አባል ከአባልነቱ ሊሰናበት የሚችለው፡-
   ሀ. ከስራው ሲለቅ፤
   ለ. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 10 ንኡስ ዓንቀፅ ለ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዕድገት ወይም በሌላ ምክንያት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ፍርድ ቤት የሄደ እንደሆነ፤
   ሐ. የጉባኤው ግዴታና ሓላፊነት በሚገባ ያልተወጣ ወይም ለተከታታይ ሦስት የጉባኤው ስብሰባዎች ያለፈቃድና ያለበቂ ምክንያት ያልቀረበ መሆኑን ጉባኤው ሲያረጋግጥና በጉባኤው ማስጠንቀቅያ ተሰጥቶት ማሻሻል ያልቻለ፤ ወይም
   መ. በከባድ የስነ ምግባር ጉድለት በጉባኤው የተቀጣ እንደሆ ነው።
2. በጉባኤው ስብሰባ የማይገኝ ኣባል ከፍርድ ቤት የተወከለ እንደሆነ በደኞች፣ሬጅስትራሮችና የጉባኤ ተሿሚዎች መተዳደርያና የስነ ምግባር ጉድለት ደንብ መሰረት ታይቶ የስነ ምግባር ጉድለት ክስ የሚቀርብበት ይሆናል።
3. ከፍርድ ቤት ውጭ የተወከለ የጉባኤው አባል ያለበቂ ምክንያት ሓላፊነቱን የማይወጣ እንደሆነ መጀመርያ በጉባኤው ሰብሳቢ በቃል ይነገረዋል፤ ካላስተካከለ በፅሑፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፤ ማሻሻል ካልቻለ ደግሞ ምክር ቤቱ እንድያውቀው ይደረጋል።

## ዓንቀፅ 12. ስልጣንን ተግባርን ጉባኤ

ጉባኤ ካብዚ ንታሕቲ ዝተዘርዘሩ ስልጣንን ተግባርን ይህልውዎ፡-

1. ብመሰረት እዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 18ን 19ን ዝተቐመጠ ረቛሒ ብመቕረባይነት ኣካቢ ጉባኤ ካብ ዝቐረቡ ብቑዓት ዝበሃሉ ሕፁያት ዳያኑን ሬጅስትራራትን መልሚሉ ንሽመት ናብ ቤት ምኽሪ የቕርብ።
2. ብመቕረባይነት ኣካቢ ጉባኤ ንተሸየምቲ ጉባኤ ይሸይም፤ የዕቢ፤ የውርድ። ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።
3. ምልመላ፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ ነዊሕ ስልጠናን ትምህርትን ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን ዝምልከት ይውስን። ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።
4. ዳይና፣ ሬጅስትራራን ተሸያሚ ጉባኤን ዝኽፈሎ መሃያ፣ እርከንን ብርኪ ዕቤትን፣ ካልኦት ጥቕማ ጥቕምን ይውስን፤ ምስ ወሰነ ተግባራዊ ይገብር። ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።
5. ስዓት ስራሕ ፣ ኣወሃህባ ፍቓድን ዕረፍትን ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን ዝምልከት ደንቢ የውፅእ።
6. ብቤት ፅሕፈት ጉባኤ ዝተዳለወ ዓመታዊ ትልሚ መርሚሩ የፅድቕ፤ ንተግባራውነቱ ይከታተል።
7. ደንቢ መተሓዳደርን ስነ-ምግባርን ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን የውፅእ።
8. ኣብ ማእኸላይን ወረዳን ቤት ፍርዲ ዝርከብ ፕረዚደንትን ምኽትል ፕረዚደንትን፣ ኣብ

## አንቀፅ 12.የጉባኤው ስልጣንና ተግባር

ጉባኤው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 18 እና 19 በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት በጉባኤው ሰብሳቢ ከቀረቡት እጩ ዳኞችና ሬጅስትራሮች መልምሎ ለሹመት ለምክር ቤት ያቀርባል።
2. በጉባኤው ሰብሳቢ አቅራቢነት የጉባኤ ተሿሚዎችን ይሾማል፤ ያሳድጋል፣ ያወርዳል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
3. የዳኛ፣ ሬጅስትራርና የጉባኤ ተሻሚን ምልመላ፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ ስልጠናና ትምህርትን በሚመለከት ይወስናል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
4. ዳኛ፣ ሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚ የሚከፈለው ደመወዝ፣ እርከንና የእድገት ደረጃ፣ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ይወስናል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
5. የዳኛ፣ የሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚን የስራ ሰዓት፣ የፈቃድ እና የዕረፍት አሰጣጥ የሚመለከት ደንብ ያወጣል።
6. በጉባኤው ፅሕፈት ቤት የተዘጋጀውን ዓመታዊ እቅድ መርምሮ ያፀድቃል፤ ተግባራዊነቱም ይከታተላል።
7. የዳኛ፣ የሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚን መተዳደሪያና የስነምግባር ደንብ ያወጣል።
8. የከፍተኛና ወረዳ ፍርድ ቤቶች ፕረዚደንቶችና ምክትል ፕረዚደንቶች፣

ዝኾነ ብርኪ ቤት ፍርዲ ዝርከብ ዳይና፣ ሬጅስትራርን ካሊእ ተሸያሚ ጉባኤን ኣፈፃፅማ ስርሖ ዝምዘነሉ መምርሒ የውፅእ፤ ተግባራውነቱ ይከታተል።

9. ኣብ ስርሖ ርኡይ ዝኾነ ምንእስ ዓቕሚ ዘርእየ ወይ ከቢድ ክሲ ጉድለት ስነ ምግባር ዝቐረቦ ዳይና ወይ ሬጅስትራር ካብ ስራሕ ክሰናብቶ ወይ ካብ ዝለዓለ ናብ ዝተሓተ ብርኪ ቤት ፍርዲ ከውርዶ ዝኽእል ምዃኑ እንተተረጋጊፁ ናብ ቤት ምኽሪ ኣቕሪቡ የወስን። ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።

10. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 9 ብቤት ምኽሪ ክሳብ ዝዉሰን ክብደት እቲ ጉዳይ ኣብ ግምት ብምእታው መሃይኡ እናተኸፈሎ ካብ ስራሕ ኣጊድዎ ክፀንሕ ይኽእል። ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።

11. ድሕንነት ከባቢ ስራሕን ጥዕናን ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን ዝተሓለወ ምዃኑ የረጋግፅ።

12. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ /4/ን/5/ን ኣብ ዝተዘርዘሩ ዋኒናት ኣመልኪቱ ንዝልዓል ጥርዓን ሰሚዑ ፍታሕ ዝህብ ኮሚቴ ሰማዒ ጥርዓን ከምኣድላይነቱ ከጣይሽ ይኽእል፣

13. ስራሕቲ ጉባኤ ንምትግባር ዝሕግዝ ኮሚቴ ከምኣድላይነቱ ካብ ውሽጢ ኣባላት ወይ ካብ ኣባላት ጉባኤ ወፃኢ እናጣየሸ ከዋፍር ይኽእል።

14. ጉድለት ስነ ምግባር ዝምልከት ክሲ

በማንኛም ደረጃ የሚገኝ ዳኛ፣ ሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚ የስራ አፈፃፀም የሚመዘንበት መመሪያ ያወጣል፤ ተግባራዊነቱም ይከታተላል።

9. በስራው ላይ ግልፅ የአቅም ማነስ ያሳየ ወይም ከባድ የስነ ምግባር ጉድለት ክስ የቀረበበት ዳኛ ወይም ሬጅስትራር ከስራው ሊያሰናብተው ወይም ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ የፍርድ ቤት እርከን ዝቅ ሊያደርገው የሚችል መሆኑን የተረጋገጠ እንደሆነ ለምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

10. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 9 በምክር ቤቱ እስኪ ወሰን ድረስ የጉዳዩን ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት ደመወዝ እየተከፈለው ከስራ አግዶት ሊቆይ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

11. የዳኛ፣ ሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚ የስራ አከባቢ ደህንነትና ጤንነት የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል።

12. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ /4/ እና /5/ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ የሚነሱ አቤቱታዎችን ወይም ቅሬታዎችን ተቀብሎ መፍትሄ የሚሰጥ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ ሊያቋቁም ይችላል።

13. የጉባኤው ስራዎች ለማከናወን የሚያግዙ ኮሚቴዎችን እንደአሰፈላጊነቱ ከአባላቱ መካከል ወይ ከአባላቱ ውጭ እያዋቀረ ማሰማራት ይችላል።

14. የስነ ምግባር ጉድለት ክስ የቀረበ እንደሆነ

እንተቐሪቡ ብኽፍሊ ስነ-ምግባርን ኢንስፔክሽንን ወይ ጊዚያዊ ኮሚቴ ብምጥያሽ ክፃረ ይገብር፤ በቲ ክፍሊ ወይ ኮሚቴ ንዘቕረበሉ ውሳነ ሓሳብ መርሚሩ ይውስን።

15. ጉባኤ ዝህቦ ውሳነ ሓሳብ ካብ ሓደ ብርኪ ናብ ዝተሓተ ብርኪ ምውራድ ወይ ምብራር እንተኾይኑ ናብ ቤት ምኽሪ የቕርብ፤ ካብዚ ወፃኢ እንተኾይኑ ድማ ናይ መወዳእታን ይግብኣኒ ዘይበሃሎን ይኸውን።

16. ኣብ ምጉልባት ነፃነትን እወንታዊ ህንፀት ምስልን ቤት ፍርዲ ኣበርክቶ ዘለዎም ስራሕቲ የሳልጥ።

17. ምስ ባህሪ ስርሑ ዝተኣሳሰሩ ካልኦት ሕጋዊ ተግባራት ይፍፅም።

**ዓንቀፅ 13. ስልጣን ተግባርን ኣካቢ ጉባኤ**

ኣካቢ ጉባኤ እዞም ዝስዕቡ ስልጣንን ተግባርን ይህልውዎ፦

1. ንቤት ፅሕፈት ጉባኤ ብላዕለዋይነት ይመርሕን ይቆፃፀርን።
2. ንኣኼባ ጉባኤ ይፅውዕ፤ ብኣካብነት ይመርሕ።
3. ብመሰረት እዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 18ን 19ን ዝተቐመጠ ረቛሒ ዳያኑ፣ ሬጅስትራራትን ተሸየምቲ ጉባኤን ዝበቕው ሓርዩ ናብ ጉባኤ የቕርብ፤ በቲ ጉባኤ ዝተመልመሉ ንሽመት ናብ ቤት ምኽሪ የቕርብ።
4. ህፁፅ ኩነታት እንተጋጥም ወይ ጉባኤ ንምእካብ ኣብ ዘፀገመሉ እዋን ኣተሓባባሪ ማእኸላይ ወይ ወረዳ ቤት ፍርዲ፣ ዳይናን ሬጅስትራርን ብግዚያዊነት ይምድብ፤ የዛውር። እዚ ዝተገበረ

በስነ-ምግባርና ኢንስፔክሽን ክፍል ወይም በጊዚያዊ ከሚቴ እንዲጣራ ያደርጋል፤ በክፍሉ ወይም በኮሚቴው የቀረበበለትን የውሳኔ ሓሳብ መርምሮ ይወስናል።

15. ጉባኤው የሚሰጠው የውሳኔ ሓሳብ ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ የፍርድ ቤት እርከን ዝቅ ማድረግ፣ ወይም ከስራው ማሰናበት ከሆነ ለምክርቤት ያቀርባል፤ ከዚህ ውጭ ከሆነ ደግሞ ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበትና የመጨረሻ ይሆናል።

16. የፍርድቤት ነፃነት ለማጠናከርና ኣወንታዊ ምስል ለመገንባት ኣስተዋፅኦ ያላቸው ስራዎችን ያከናውናል።

17. ከስራው ባህሪ ጋር የተያየዙ ሌሎች ሕጋዊ ተግባራትን ይፈፅማል።

**አንቀፅ 13. የጉባኤው ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር**

የጉባኤ ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የጉባኤውን ፅህፈት ቤት በበላይነት ይመራል።
2. የጉባኤው ስብሰባ ይጠራል፤ በሰብሳቢነት ይመራል።
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 እና 19 በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት ለዳኝነትና ሬጅስትራርነት ብቁ የሆኑትን መርጦ ለጉባኤው ያቀርባል፣ በጉባኤው የተመለመሉትን ለሹመት ለምክር ቤት ያቀርባል።
4. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ጉባኤው ለመሰብሰብ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ የከፍተኛ ወይም የወረዳ ፍርድ ቤት አስተባባሪ፣ ዳኞች እና ሬጅስትራሮች

ግዚያዊ ዝውውርን ምደባን ኣብ ዝቕፅል ኣኼባ ንከፅድቖሉ ናብ'ቲ ጉባኤ የቕርብ።

5. ብድልየቱ ዝለቕቕ ዳይና ወይ ሬጅስትራር ዝሃቦ ገደብ መጠንቀቕታ ግዜ ምስኣኸለ መልቀቒ ወረቐት ይህብ፤ ኣብ ቀፃሊ ኣኼባ ድማ ነቲ ጉባኤ ይፍልጥ።
6. ብቦርድ ሓካይም ካብ ስራሕ ክሰናበት ንዝተወሰነሉ ዳይና፣ ሬጅስትራር ወይ ተሸያሚ ጉባኤ ደብዳቤ ስንብት ይህብ።
7. ብናይ ባዕሉ ተበግሶ ወይ ብዝረኸቦ ሓበሬታ ኣብ ዝኾነ ብርኪ ቤት ፍርዲ ዝተረኣየ ጉድለት ስነ ምግባር ተፃርዩ ውሳነ ንክረክብ ናብ ጉባኤ የቕርብ።
8. ንጉባኤ ዝተወሃበ ስልጣን ሕልው ኮይኑ ብከቢድ ጉድለት ስነ ምግባር ዝተኸሰሰ ዳይና፣ ሬጅስትራር ወይ ተሸያሚ ጉባኤ ኣድላይ ኮይኑ እንተረኺብዎ ካብ ስራሕ ኣጊድዎ ክፀንሕ ይኽእል፣ኣብ ዝቕፅል ኣኼባ ድማ ነቲ ጉባኤ የፍልጥ።
9. ንዳይነት ዝተመልመለ ሕፁይ ዳይና ወይ ሬጅስትራር ሸመቱ ብቤት ምኽሪ ክሳብ ዝፀድቕ ኣብ ቤት ፍርዲ ብሓጋዛይነት እናሰርሐ ክፀንሕ ይገብር።
10. ናይቲ ጉባኤ ውሳነታት ተግባራውነት ይከታተልን ይቆፃፀርን፣ ነቲ ጉባኤ ወኪሉ ይሰርሕ።

**ዓንቀፅ 14.** <u>**ምጥያሽ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ**</u>

ስራሕቲ ጉባኤ ንምስላጥ ዝሕግዝ ቤት ፅሕፈት

በጊዚያውነት ይመድባል፤ ያዛውራል። የተደረገውን ጊዚያዊ ዝውውርና ምደባ በሚቀጥለው ስብሰባ እንዲፀድቅለት ለጉባኤው ያቀርባል።

5. በፍላጎቱ ከስራ የሚለቅ ዳኛ ወይም ሬጅስትራር የሰጠውን የማስጠንቀቅያ ጊዜ ገደብ ሲደርስ የመልቀቂያ ደብዳቤ ይሰጣል፤ በሚቀጥለው ስብሰባም ለጉባኤው ያሳውቃል።
6. በሓኪሞች ቦርድ ከስራ እንዲሰናበት ለተወሰነለት ዳኛ፣ ሬጅስትራር ወይም የጉባኤ ተሿሚ የስንብት ደብዳቤ ይሰጣል።
7. በራሱ ተነሳሽነት ወይም ባገኘው ጥቆማ መሰረት በማንኛውን የፍርድቤት ደረጃ የሚታይ የስነ-ምግባር ጉድለት ተጣርቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ለጉባኤው ያቀርባል።
8. ለጉባኤው የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በከባድ የስነምግባር ጉድለት የተከሰሰ ዳኛ፣ ሬጅስትራር ወይም የጉባኤ ተሿሚ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከስራ ታግዶ እንዲቆይ ያደርጋል፤ በሚቀጥለው ስብሰባ ለጉባኤው ያሳውቃል።
9. ለዳኝነት ወይም ለሬጅስትራርነት የተመለመለ እጩ ዳኛ ወይም እጩ ሬጅስትራር ሹመቱ በምክር ቤቱ እስኪፀድቅ ድረስ በፍርድቤት በረዳትነት እየሰራ እንዲቆይ ያደርጋል።
10. የጉባኤው ውሳኔዎችን ተግባራዊነት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ጉባኤውን ወክሎ ይሰራል።

**አንቀፅ 14.** <u>**የጉባኤው ፅሕፈት ቤት መቋቋም**</u>

የጉባኤው ስራዎች ለማከናወን የሚያግዝ የጉባኤ

ጉባኤ በዚ ኣዋጅ ተጣይሹ ኣሎ።

**ዓንቀፅ 15. ስልጣንን ተግባርን ቤት ፅሕፈት ጉባኤ**

ቤት ፅሕፈት ጉባኤ እዞም ዝስዕቡ ስልጣንን ተግባርን ይህልውዎ።

1. ዓመታዊ ትልምን በጀትን ጉባኤ ኣዳልዩ የቕርብ።
2. ውሳነታት ጉባኤ ይከታተል፤የፈፅም።
3. ናይቲ ጉባኤ ከይዲ ስራሕቲ ናይ ስራሕ ሃዋህው የመቻቹ፤ ናብ ስራሕ የዋፍር፤ መዝገብን ሰነድን ብኣግባቡ ይሕዝ።
4. ኣብ ልዕሊ ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን ዝቐርብ ጥርዓን ወይ ክሲ ጉድለት ስነ ምግባር ብምቕባል ንኣካቢ ጉባኤ የቕርብ፤
5. ውልቀ ማህደር ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን ይውድብ፤ ዘድሊ መረዳእታ ዝተተሓሓዘ ምዃኑ ይከታተል፤ ብዝምልከቶ ኣካል ተደላይ ኣብ ዝኾነሉ የቕርብ።
6. ምዘና ኣፈፃፅማ ስራሕ ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን ጉባኤ ብዘውፅኦ መዕቀኒ መሰረት ብቐፃልነት ዝሳለጥ ዘሎ ምዃኑ የረጋግፅ፤ ውፅኢት ምዘና ኣፈፃፅማ ስራሕ ብእዋኑ ምስ ውልቀ ማህደር ዳይና ክተሓሓዝ ይገብር።
7. ስራሕቲ ጉባኤ ንምዝማን፤ ኣፈፃፅማ ስራሕቱ ንምዕባይን ህዝባዊ እምነት ዘርክቡን ስራሕቲ ይምህዝ፣ የተግብር።

ፅሕፈት ቤት በዚህ ኣዋጅ ተቋቁሟል።

**አንቀፅ15. የጉባኤው ፅሕፈት ቤት ስልጣንና ተግባር**

የጉባኤው ፅሕፈት ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. የጉባኤው ዓመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ያቀርባል።
2. የጉባኤው ውሳኔዎችን ይከታተላል፤ ያስፈፅማል።
3. የጉባኤው የስራ ሂደቶችን የስራ ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ ወደ ስራ ያሰማራል፤ መዝግብና ሰነድ በኣግባቡ ይይዛል።
4. በዳኛ፣ ሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም የስነ-ምግባር ጉድለት ክስ በመቀበል ለጉባኤው ሰብሳቢ ያቀርባል።
5. የዳኛ፣ የሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚ የግል ማህደር ያደራጃል፤ አስፈላጊ ማስረጃ የተያያዘ መሆኑን ይከታተላል፤ በሚመለከተው ኣካል ሲፈለግ ያቀርባል።
6. ጉባኤው ባወጣው መስፈርት መሰረት የዳኛ፣ የሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚ የስራ አፈፃፀም ምዘና በቀጣይነት እየተከናወነ መሆኑን ያረጋግጣል፤ የስራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቱ በጊዜው ከግል ማህደር እንዲያያዝ ያደርጋል።
7. የጉባኤው ስራዎች ለማዘመን፤ የስራ አፈፃፀሙ የሚያሳድጉና የህዝብ እምነት የሚያስገኙ ስራዎች ይቀርፃል፤ ይተገብራል።

## ዓንቀፅ 16. ስልጣንን ተግባርን ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ

ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ ተፀዋዕነቱ ንኣካቢ ጉባኤ ኮይኑ እዞም ዝስዕቡ ስልጣንን ተግባርን ይህልውዎ፦

1. ንቤት ፅሕፈት ጉባኤ ዝተወሃበ ስልጣንን ሓላፍነትን ይከታተል፣ ይትግብር።
2. ዓመታዊ ረቂቕ ትልምን ፀብፃብ ኣፈፃፅማ ስራሕን ጉባኤ የዳሉ።
3. ምስ ኣካቢ ጉባኤ ብምዝርራብ ኣጀንዳ ኣኼባ የዳሉ፤ ንኣባላት ጉባኤ መፀዋዕታ ይልእኽ።
4. ናይቲ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ይሕዝ፤ ሕድሕድ ኣባል ጉባኤ ዝፈረመ ምዃኑ የረጋግፅ።
5. ስራሕቲ ከይዲ ስራሕቲ እቲ ቤት ፅሕፈት ይከታተል፤ የፈፅም።
6. ብዳይና፣ ሬጅስትራር ወይ ተሸያሚ ጉባኤ ዝቐርብ ጥርዓን ተቐቢሉ ናይቲ ጥርዓን ትሕዝቶን ውሳነ ሓሳብን ብምድላው ንኣካቢ ጉባኤ የቕርብ፤ እንትውሰን የፈፀም።
7. ሰራሕተኛታት ቤትፅሕፈት ይቆፃፀር፤ የመሓድር።
8. ምስ ኣካቢ ጉባኤ ብምምኻር ምምሕያሽ መሃያን ካልኦት ጥቕማ ጥቕምን ዳይና፣ ሬጅስትራር ወይ ተሸያሚ ጉባኤ ክፅናዕ ብምግባር ውሳነ ሓሳብ ኣዳልዩ ናብ ኣካቢ ጉባኤ ክቐርብ ይገብር።

## አንቀፅ 16. የጉባኤው ፅሕፈት ቤት ሓላፊ ስልጣንና ተግባር

የጉባኤው ፅሕፈት ቤት ሓለፊ ተጠሪነቱ ለጉባኤው ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

1. ለጉባኤው ፅሕፈት ቤት የተሰጠው ስልጣንና ሓለፊነት ይከታተላል፤ ይተገብራል።
2. የጉባኤው ዓመታዊ ረቂቅ እቅድና የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል።
3. ከጉባኤው ሰብሳቢ በመነጋገር የጉባኤው የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤ ለጉባኤው አባላት የስብሰባ ጥሪ ይልካል።
4. የጉባኤው ቃለ ጉባኤ ይይዛል፤ እያንዳንዱ የጉባኤው ስብሰባ ተሳታፊ አባል የፈረመ መሆኑን ያረጋግጣል።
5. የፅሕፈት ቤቱ የስራሂደቶች ስራዎችን ይከታተላል፤ ያስፈፅማል።
6. በዳኛ፣ ሬጅስትራር ወይም የጉባኤ ተሿሚ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀብሎ ያስተናግዳል፤ የአቤቱታው ይዘትና ውሳኔ ሓሳብ በማዘጋጀት ለጉባኤው ሰብሳቢ ያቀርባል፤ ሲወሰን ያስፈፅማል።
7. የፅሕፈት ቤቱ ሰራተኞችን ይቆጣጠራል፤ ያስተዳድራል።
8. ከጉባኤው ሰብሳቢ በመመካከር የዳኛ፣ ሬጅስትራር ወይም የጉባኤ ተሿሚ የደመወዝ ማሻሻያ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን አስጠንቶ የውሳኔ ሓሳብ አዘጋጅቶ ለጉባኤው ሰብሳቢ ያቀርባል።

9. ብጉባኤ ወይ ብኣካቢ ጉባኤ ዝወሃቦ ካሊእ ተዛማዲ ስራሕ ይሰርሕ።

**ዓንቀፅ 17. ኣወዳድባ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ**

1. ቤት ፅሕፈት ጉባኤ በዚ ኣዋጅን ብካሊእ ሕግን ዝተወሃቦ ስልጣንን ሓላፍነትን ብኣግባቡ ንምፍፃም ብዘኽእልዎ ከይዲ ስራሕቲ ዝተወደበ ኣወዳድባ ይህልዎ።
2. ሕድሕድ ከይዲ ስራሕ ኣድለይቲ ዝኾኑ ናይ ባዕሉ ሰራሕተኛታት ዝህልዎ ኮይኑ ካብ ሓላፊ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ ዝወሃቦ ስራሕ ይፍፅም።
3. ሕድሕድ ከይዲ ስራሕ ቤት ፅሕፈት ጉባኤ ዝህልዎ ስራሕን ሓላፍነትን ብዝፀድቕ መሓውር ይውሰን።

**ክፍሊ ኣርባዕተ**

**ምልመላ፣ ሽመት፣ ስንብትን ካልኦት መሰላትን ዳይና፣ ሬጅስትራርን ተሸያሚ ጉባኤን**

**ዓንቀፅ 18. ንሽመት ዳይነት ዘብቅዑ ረቛሕታት**

1. እዞም ዝስዕቡ ረቛሒታት ዘማልአ ሰብ ተወዳዲሩ ንስራሕ ዳይነት ክሽየም ይኽእል፡-

ሀ. ኢትዮጵያዊ ዝኾነ፣

ለ. ብሞያ ዳይነት ንምስራሕ ፍቃደኛ ዝኾነ፣

ሐ. ዕድሚኡ ካብ 25 ዓመት ዘይንእስ ፣

መ. ንሕገ-መንግስቲ ፌደራልን ክልልን ተኣማኒ ዝኾነ፣

ረ. ቋንቋ ስራሕ እዚ ክልል ብዝግባእ ዝፈልጥ፣

9. በጉባኤው ወይም በጉባኤው ሰብሳቢ የሚሰጠው ሌላ ተዛማጅ ስራ ይሰራል።

**አንቀፅ 17. የጉባኤው ፅሕፈት ቤት አደረጃጀት**

1. የጉባኤው ፅሕፈት ቤት በዚህ አዋጅና በሌላ ሕግ የተሰጠውን ስልጣንና ሓላፊነት በአግባቡ ለመፈፀም በሚያስችሉት የስራ ሂደቶች የተዋቀረ አደረጃጀት ይኖረዋል።
2. እያንዳንዱ የስራ ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የራሱ ሰራተኞች የሚኖሩት ሲሆን በጉባኤው ፅሕፈት ቤት ሓላፊ የሚሰጠውን ስራ ይፈፅማል።
3. እያንዳንዱ የጉባኤው ፅሕፈት ቤት የስራ ሂደት የሚኖረው ሃላፊነት በሚፀድቀው መዋቅር ይወሰናል ።

**ክፍል አራት**

**የዳኛ፣ ሬጅስትራርና የጉባኤ ተሿሚ ምልመላ ፣ ሹመት፣ ስንብትና ሌሎች መብቶች**

**አንቀፅ 18. ለዳኝነት ሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች**

1. የሚከተሉት መመዘኛዎች ያሟላ ሰው ተወዳድሮ ለዳኝነት ስራ ሊሾም ይችላል።

ሀ. ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ. በዳኝነት ሙያ ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፣

ሐ. ዕድሜው ከ25 ዓመት የማያንስ፣

መ. ለፌደራልና ለክልሉ ሕገ መንግስት ታማኝ የሆነ፣

ረ. የክልሉ የስራ ቋንቋ በሚገባ የሚያውቅ፣

ሰ. ኣፍልጦ ካብ ዘለዎ ላዕለዋይ ትካል ትምህርቲ ብሕጊ እንተነኣሰ ቀዳማይ ዲግሪ ዘለዎ ኮይኑ ናይ ላዕለዋይ ትካል ትምህርቲ መውፅኢ ፈተና ዝሓለፈ፣

ሸ. ቅድመ ስራሕ ስልጠና ዳይነት ዝወሰደ፣

ቀ. ፅቡቅ ስነ-ምግባር ዘለዎ ምኳኑ መረዳእታ ዘቕርብ፣

በ.ንስርሑ ዘዕንቅፍ ፀገም ጥዕና ዘይብሉ ምኳኑ መረዳእታ ዘቕርብ፣

ተ. ካብ ዝተፈላለዩ መዐወኒ እፃትን ካልኦት መነወርቲ ተግበራትን ናፃ ዝኾነን፣

ቸ. ኣባል ዝኾነ ፖለቲካዊ ውድብ ዘይኮነን እዩ፣

ነ. ብኸቢድ ገበን ተቐፂዑ ዘይፈልጥ ወይ ብቐሊል ገበን ተቐፂዑ እንተነይሩ 'ውን ዝተሰየመ ምኳኑ መረዳእታ ዘቕርብ፣

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1/ሸ/ ዝተጠቀሰ እንተሃለወ'ውን ካልኣይ ዲግሪን ልዕሊኡን ብሕጊ ዝተመሃረ ኮይኑ በቲ ሞያ ክልተ ዓመት ስራሕ ልምዲ ዘለዎ ወይ ቀዳማይ ዲግሪ ሒዙ እንተነኣሰ በቲ ሞያ ናይ ሰለስተ ዓመት ልምዲ ስራሕ ዘለዎ እንተኾይኑ ብቐጥታ ክሽየም ይኽእል። ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።

ዓንቀፅ 19.<u>ንረጅስትራርነት ዘብቅዑ ረቛሕታት</u>

1. እዞም ዝስዕቡ ረቛሕታት ዘማልእ ሰብ ተወዳዲሩ ንስራሕ ሬጅስትራርነት ክሽየም

ሰ. እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ቢያንስ የመጀመርያ ዲግሪ ያለውና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መውጫ ፈተና ያለፈ፣

ሸ. የዳኝነት የቅድመ ስራ ስልጠና የወሰደ፣

ቀ.ጥሩ ስነ-ምግባር ያለው መሆኑን ማስረጃ የሚያቀርብ፣

በ. ስራውን ለማከናወን የማያስችል የጤና ችግር የሌለበት መሆኑን ማስረጃ የሚያቀርብ፣

ተ. ከተለያዩ ኣደንዛዥ እፆችና ሌሎች አስነዋሪ ተግባራት ነፃ የሆነ፣

ቸ. የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ኣባል ያልሆነ ነው፣ .

ነ.በከባድ ወንጀል ተቀጥቶ የማያውቅ እንዲሁም ብቀላል ወንጀል ተቀጥቶ የነበረ እንደሆነ የተሰየመ መሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብ፣

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1/ሸ/ የተጠቀሰው ቢኖርም ሁለተኛ ዲግሪና ከዚያ በላይ በህግ የተማረ ሆኖ በሙያው የሁለት ዓመት የስራ ልምድ ያለው ወይም የመጀመርያ ዲግሪ ኖሮት ቢያንስ በሙያው የሶስት ዓመት የስራ ልምድ ያለው በቀጥታ ሊሾም ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

አንቀፅ19. <u>ለረጅስትራርነት የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

1. የሚከተሉት መመዘኛዎች ያሟላ ሰው ተወዳድሮ ለሬጅስትራርነት ስራ ሊሾም

ይኽእል።

ሀ. ኢትዮጵያዊ ዝኾነ፣

ለ. ብሬጅስትራርነት ስራሕ ንምስራሕ ፍቃደኛ ዝኾነ፣

ሐ. ንሕገ-መንግስቲ ፌደራልን ክልልን ተኣማኒ ዝኾነ፣

መ. ቋንቋ ስራሕ እዚ ክልል ብዝግባእ ዝፈልጥ፣

ረ. ኣፍልጦ ካብ ዘለዎ ላዕለዋይ ትካል ትምህርቲ ብማሕበራዊ ሳይንስ እንተነኣሰ ቀዳማይ ዲግሪ ዘለዎ፣

ሰ. ፅቡቕ ስነ-ምግባር ዘለዎ ምኻኑ መረዳእታ ዘቕርብ፣

ሸ. ካብ ደንቢ ምትሕልላፍ ወፃእ ብገበን ተቐፂዑ ዘይፈልጥ ወይ ተቐፂዑ እንተነይሩ ዝተሰየመ ምኻኑ መረዳእታ ዘቕርብ፣

ቀ. ስርሑ ዘዕንቅፍ ፀገም ጥዕና ዘይብሉ ምኻኑ መረዳእታ ዘቕርብን፣

በ. ካብ ዝተፈላለዩ መዐወኒ እፃትን ካልኦት መነወርቲ ተግባራትን ናፃ ዝኾነን እዩ።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስዓንቀፅ 1 ዘሎ ዝርዝር ኣፈፃፅምኡ ብደንቢ ይውሰን።

**ንቀፅ 20.** **<u>ቃለ መሓላ</u>**

1. ዳያኑ ቅድሚ ስራሕ ምጅማሮም ዝስዕብ ቃለ-መሓላ ይፍፅሙ።

"ኣነ........በዚ ሎሚ ዕለት ዳይና.........ቤት ፍርዲ ኾይነ ተሸይመ ሰርሐይ እንትጅምር ዝተወሃበኒ

---

ይችላል።

ሀ.ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ. በሬጅስትራርነት ስራ ለመስራት ፈቃደኛ የሆነ፣

ሐ. ለፌደራልና ለክልሉ ሕገ መንግስት ታማኝ የሆነ፣

መ. የክልሉ የስራ ቋንቋ በሚገባ የሚያውቅ፣

ረ. እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በማሕበራዊ ሳይንስ ቢያንስ የመጀመርያ ዲግሪ ያለው፣

ሰ. ጥሩ ስነ-ምግባር ያለው መሆኑን ማስረጃ የሚያቀርብ፣

ሸ. ከደንብ መተላለፍ ውጭ በወንጀል ተቀጥቶ የማያውቅ ወይም ተቀጥቶ የነበረ እንደሆነም የተሰየመ መሆኑ ማስረጃ የሚያቀርብ፣

ቀ. ስራውን ለማከናወን የማያስችል የጤና ችግር የሌለበት መሆኑን ማስረጃ የሚያቀርብ፤ እና

በ. ከተለያዩ ኣደንዛዥ እፆችና ሌሎች ኣስነዋሪ ተግባራት ነፃ የሆነ ነው።

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 ያለው ዝርዝር ኣፈፃፀም በደንብ ይወሰናል።

**አንቀፅ 20.** **<u>ቃለ መሓላ</u>**

1.ማንኛውም ዳኛ ስራውን ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ መሓላ ይፈፅማል።

"እኔ.......በዛሬው እለት የ...... ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኜ ስሾምና ሰራየን ስጀምር የተሰጠኝን ከፍተኛ

ዓብይ ሓላፍነት ንሕገ-መንግስቲ ተገዛኣይ ብምዃን ብሕጊ ጥራሕ እናተመራሕኹ ስነ-ምግባረይ ሓልየ ስርሐይ ብተኣማንነት ንክፍፅም ቃል ይኣቱ።"

2. ሬጅስትራራት'ውን ቅድሚ ስራሕ ምጅማሮም ብተመሳሳሊ ኣገባብ ቃለ መሓላ ክፍፅሙ ይግበር።

**ዓንቀፅ 21.ስንብት ስራሕ**

1. ዝኾነ ዳይና ወይ ሬጅስትራር ካብ ስርሑ ክሰናበት ዝኽእል በዞም ዝስዕቡ ምኽንያታት ጥራሕ'ዩ።

ሀ. ብውልቀ ድልየቱ ስርሑ ክለቕቕ ዝደለየ ዳይና እንተኾይኑ ናይ ክልተ ወርሒ፣ ሬጅስትራር ድማ ናይ ሓደ ወርሒ ናይ ፅሑፍ መጠንቀቕታ ንጉባኤ ብምሃብ፤

ለ. ብምኽንያት ሕማም ስርሑ ብዝግባእ ክፍፅም ከምዘይኽእል ዘረድእ ውሳነ ቦርድ ሓኻይም እንተቕርብ፤

ሐ. ብመሰረት መምርሒ መፅቀኒ ኣፈፃፅማ ስራሕ ርኡይ ዝኾነ ናይ ስራሕ ብቕዓትን ቅልጣፈን ዝነኣሰ ምዃኑ ጉባኤ እንትውስን፤

መ. ካብ ስራሕ ከባርር ዘኽእል ከቢድ ጉድለት ስነ ምግባር ወይ ንስራሕ ዳይነት ብባህሪኡ ዝፃባእ ተግባር ገበን ብምፍፃሙ ጥፍኣተኛ ተባሂሉ ካብ ስራሕ ክሰናበት ጉባኤ እንትውስን ወይ፤

ረ. ብሕጊ ዝተወሰነ ናይ ጡረታ ዕድመ እንትበፅሕ 'ዩ።

ሃለፊነት ለህገ መንግስቱ ተገዥ በመሆን በህግ ብቻ እየተመራሁኝ ስነ-ምግባሬን ጠብቄ በታማኝነት ለመፈፀም ቃል እገባለሁ"

2. ሬጅስትራርም ስራው ከመጀመሩ በፊት በተመሳሳይ ሁኔታ ቃለ ማሓላ እንዲፈፅም ይደረጋል።

**አንቀፅ 21.የስራ ስንብት**

1.ማንኛውም ዳኛ ወይ ሬጅስትራር ከስራው ሊሰናበት የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው።

ሀ.በራሱ ፈቃድ ስራውን መልቀቅ የፈለገ ዳኛ ከሆነ የሁለት ወር፣ ሬጅስትራር ደግሞ የአንድ ወር የፅሑፍ ማስጠንቀቅያ በመስጠት፤ ወይም

ለ. በህመም ምክንያት ስራውን በሚገባ ማከናወን የማይችል መሆኑን የሚያስረዳ የሓኪሞች ቦርድ ውሳኔ ሲያቀርብ፣ ወይም

ሐ. በስራ አፈፃፀም መመዘኛ መመሪያ መሰረት ግልፅ የሆነ የስራ ብቃትና ቅልጥፍና ያነሰው መሆኑን ጉባኤው ሲወስን፤ ወይም

መ. ከስራ ሊያባርር የሚያስችል ከባድ የስነ-ምግባር ጉድለት ወይም በባህሪው የዳኝነት ስራን የሚፃረር የወንጀል ተግባር በመፈፀሙ ጥፋተኛ ተብሎ ከስራ እንዲሰናበት ጉባኤው ሲወስን፤ ወይም

ረ. በሕግ የተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ሲደርስ ነው።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ1/ሀ/ዝተደንገገ እንተሃለወ'ውን ክሲ ጉድለት ስነ-ምግባር ዝቐረቦ እንተኾይኑ ናይ ስንብት ደብዳቤ ክወሃብ ዝኽእል ዝቐረቦ ክሲ ጉድለት ስነ-ምግባር ተፃርዩ ዕልባት ምስ ረኸበ እዩ።
3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝተመልከተ እንተሃለወ'ውን ኮይኑ ናይ ስንብት ደብዳቤ ዘእተወን ክሲ ጉድለት ስነ-ምግባር ዝቐረቦን ዳይና፣ ሬጅስትራር ወይ ተሸያሚ ጉባኤ እቲ ዝቐረቦ ክሲ ብሕጊ ኣብ ዝተወሰነ ግዘ ዕልባት እንተዘይረኺቡ እቲ ክሲ ጉድለት ስነ-ምግባር ከምዘይቀረቦ ተሓሲቡ መልቀቒ ደብዳቤ ይወሃቦ። ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።
4. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ኣንቀፅ 1/ሐ/ን/መ/ን ዝተመልከተ ኣብ ልዕሊ ዳይናን ሬጅስትራርን ተፈፃሚነት ዝህልዎ ናይቲ ጉባኤ ውሳነ ናብ ቤት ምኽሪ ቐሪቡ እንትፀድቕ'ዩ።

**ዓንቀፅ 22.** **<u>ኣወሃህባ ደብዳቤ ስንብትን ትሕዝትኡን</u>**

1. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 21 ንኡስ ዓንቀፅ 1 /ሀ/ ዝተቐመጠ ናይ ግዘ ገደብ ምስ ኣኸለ ሽዑ ንሽዑ ብኣካቢ ጉባኤ ናይ ስንብት ደብዳቤ ይወሃቦ።
2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገገ እንተሃለወ'ኳ እቲ ጉባኤ ንስራሕ ፀገም ዘይፈጥር ኮይኑ እንተረኺብዎን ኣብ ሞንጉኡ እንተተኣኪቡን እቲ ገደብ ግዘ መጠንቀቕታ ቅድሚ ምእኻሉ ስንብት ደብዳቤ ክህብ ይኽእል።
3. ዝርዝር ትሕዝቶ ስንብት ደብዳቤ እንታይ ክኸውን ከምዘለዎ ብደንቢ ይውሰን።

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1/ሀ/ የተደነገገ ቢኖርም የስነ-ምግባር ጉድለት ክስ የቀረበበት ከሆነ የስንብት ደብዳቤ ሊሰጠው የሚችል የቀረበበት የስነ-ምግባር ጉድለት ክስ ተጣርቶ ዕልባት ካገኘ በኋላ ነው።
3. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የመልቀቂያ ደብዳቤ ያስገባና የስነ ምግባር ጉድለት ክስ የቀረበበት ዳኛ፣ ሬጅስትራር ወይም የጉባኤ ተሿሚ ጉዳዩ በሕግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ዕልባት ካላገኘ የስነ-ምግባር ጉድለት ክስ እንዳልቀረበበት ታስቦ የመልቀቅያ ደብዳቤ ይሰጠዋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
4. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1/ሐ/ና/መ/ የተመለከተው በዳኞችና ሬጅስትራሮች ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረው የጉባኤው ውሳኔ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ሲፀድቅ ነው።

**አንቀፅ 22.** **<u>የስንብት ደብዳቤ አሰጣጥና ይዘቱ</u>**

1. በዚህ ኣዋጅ አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀፅ 1/ሀ/ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲደርስ ወድያውኑ በጉባኤው ሰብሳቢ የስንብት ደብዳቤ ይሰጠዋል።
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገ ቢኖርም ጉባኤው ለስራ ችግር የማይፈጥር ሆኖ ካገኘውና በዚህ መሃልም የተሰበሰበ እንደሆነ የማስጠንቀቅያው ጊዜ ገደብ ከመድረሱ በፊት ሊያሰናብተው ይችላል።
3. የስንብት ደብዳቤው ዝርዝር ይዘት ምን መሆን እንዳለበት በደንብ ይወሰናል።

ዓንቀፅ 23. ፍትሃብሄራዊ መሰል ዘይምኽሳስ ዳይና

1. ኣብ ዝኾነ ብርኪ ዝርከብ ዳይና ብዝሃቦ ዳይነታዊ ውሳነ ምኽንያት ክሲ ፍትሃብሄር ኣይቐርቦን ።

ክፍሊ ሓሙሽተ

ዝተፈላለዩ ሕጋገታት

ዓንቀፅ 24. ኣቀራርባ ክሲ ጉድለት ስነምግባር

1. ዝኾነ ሰብ ጉድለት ስነ ምግባር ፈፂሙ እዩ ኣብ ልዕሊ ዝበሎ ዳይና፣ ሬጅስትራር ወይ ተሻያሚ ጉባኤ ጥቆማ፣ ጥርዓን ወይ ክሲ ጉድለት ስነ ምግባር ናይ ምቕራብ መሰል ኣለዎ።

2. ኣብ ዝኾነ ብርኪ ቤት ፍርዲ ዝርከብ ፕረዚደንት ወይ መተሓባበሪ ክሲ ጉድለት ስነ ምግባር ናይ ምቕባል፤ ክምዝተቐበለ ንከሳሲ መረጋገፂ ናይ ምሃብን ኣብ ውሽጢ 10 መዓልቲ ንዝቐረበ ክሲ ናብ ጉባኤ ናይ ምልኣኽን ግቡእ ኣለዎ።

3. ጉባኤ ክሲ ጉድለት ስነ-ምግባር ኣብ ዘፃርየሉ ወይ ኣብ ዝውስነሉ እዋን ዘድልዩ ምስክር ወይ መረዳእታ ንምቕራብ ስሩዕ ቤት ፍርዲ ዝኽተሎ ድንጋገታት ፍትሃብሄር ስነ ስርዓት መሰረት ብምግባር ክእዝዝ ይኽእል።

4. ኣቀራርባ፣ ከይዲ ኣሰማምዓን ኣወሳስናን ክሲ ጉድለት ስነ-ምግባር ዝምርሓሉ ስነስርዓት ብደንቢ ይውሰን።

አንቀፅ 23. ፍታብሄረዊ የዳኞች ያለመከሰስ መብት

1. በማንኛውም የፍርድ ቤት እርከን የሚገኝ ዳኛ በሰጠው የዳኝነት ውሳኔ ምክንያት የፍትሃብሄር ክስ አይቀርብበትም።

ክፍል ኣምስት

የተለያዩ ድንጋጌዎች

አንቀፅ 24. የስነምግባር ጉድለት ክስ አቀራረብ

1. ማንኛውም ሰው የስነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሟል በሚለው ዳኛ፣ ሬጅስትራር ወይም የጉባኤ ተሿሚ ላይ ጥቆማ፣ አቤቱታ ወይም የስነ ምግባር ጉድለት ክስ የማቅረብ መብት አለው።

2. በማንኛውም የፍርድ ቤት እርከን የሚገኝ ፕረዚደንት ወይም አስተባባሪ የስነ ምግባር ጉድለት ክስ የመቀበል፤ የተቀበለ መሆኑን ለከሳሹ ማረጋገጫ የመስጠትና የቀረበውን ክስ በ10 ቀናት ውስጥ ወደ ጉባኤው የመላክ ግዴታ አለበት።

3. ጉባኤው የስነምግባር ጉድለት ክስ በሚያጣራበት ወይም በሚወስንበት ጊዜ የሚያስፈልገው ምስክር ወይም ማስረጃ ለማቅረብ መደበኛ ፍርድ ቤት የሚከተለውን የፍትሃብሄር ስነስርዓት ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ሊያዝ ይችላል።

4. የስነ ምግባር ጉድለት ክስ አቀራረብ፣ የመስማት ሂደትና አወሳሰን የሚመራበት ስነ-ስርዓት በደንብ ይወሰናል።

**ዓንቀፅ 25. <u>ደንብን መመርሕን ናይ ምውፃእ ስልጣን</u>**

ነዚ ኣዋጅ መተግበሪ ዝኸውን ደንብን መመርሕን ናይ ምውፃእ ስልጣን ናይቲ ጉባኤ'ዩ።

**ዓንቀፅ 26. <u>መሰጋገሪ ሕጋገታት</u>**

1. እዚ ኣዋጅ ቅድሚ ምሕታሙ ኣብ ከይዲ ዝነበረ ዝኾነ ዓይነት ክሲ ጉድለት ስነ ምግባር በቲ ነባር ደንብን መምርሕን መሰረት መዕለቢ ይረክብ።
2. ነዚ ኣዋጅ መፈፀሚ ዝኸውን ደንብን መምርሕን ክሳብ ዝወፅእ ኣብ ስራሕ ዝነበሩ ደንብን መምርሕን ነዚ ኣዋጅ ክሳብ ዘይተጻረሩ ተፈፃምነት ይህልዎም።

**ዓንቀፅ 27. <u>ዝተሰዓሩን ተፈፃምነት ዘይብሎምን ሕግታት</u>**

1. ተመሓይሹ ዝወፀ ኣዋጅ ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ቑፅሪ 244/2006 በዚ ኣዋጅ ተሳዒሩ ኣሎ።
2. ነዚ ኣዋጅ ዝፃባእ ዝኾነ ሕጊ፣ ልማዳዊ ኣሰራርሓ ወይ ኣሰራርሓን ውሳነን ተፈፀሚነት ኣይህልዎን።

**ዓንቀፅ 28. <u>እዚ ኣዋጅ ዝፀንዐሉ እዋን</u>**

እዚ ኣዋጅ ካብ ዝፀደቐሉ ዕለት 09/02//2012 ዓ/ም ጀሚሩ ዝፀንዐ ይኸውን።

ደብረፅዮን ገብረሚካኤል/ዶ/ር/

ናይ ትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ

ምክትል ፕረዚደንት

ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል /ፒ.ኤች.ዲ/
ም/ርእሰ ምምሕዳር

**አንቀፅ 25. <u>ደንብና መመሪያን የማውጣት ስልጣን</u>**

ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብና መመሪያን የማውጣት ስልጣን የጉባኤው ነው።

**አንቀፅ 26. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በሂደት ላይ የነበረ ማንኛውም ዓይነት የስነ-ምግባር ጉድለት ክስ በነባሩ ደንብና መመሪያ ዕልባት ያገኛል።
2. ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ የሚሆን ደንብና መመሪያ እስኪወጣ በስራ ላይ የነበሩ ደንብና መመሪያዎች ለዚህ አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

**አንቀፅ 27. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>**

1. ተሻሽሎ የወጣው የዳኞች አስተዳዳር ጉባኤ አዋጅ ቁጥር 244/2006 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር ወይም ውሳኔ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**አንቀፅ 28. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከፀደቀበት ከቀን 09/02/2012 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል

ደብረፅዮን ገብረሚካኤል/ዶ/ር/

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ምክትል ፕረዚደንት

ደብረፅዮን ገ/ሚካኤል /ፒ.ኤች.ዲ/
ም/ርእሰ መስተዳድር